# ዳቦውን የሰጠው ማነው?

ዮሐ.6:1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ፤ እርሱም የጥብርያዶስ ባሕር ነው። 2 በበሽተኞችም ያደረገውን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት። 3 ኢየሱስም ወደ ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ። 5 ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን። እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው። 6 ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ። 7 ፊልጶስ። እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት። 8 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ። 9 አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው።

10 **ኢየሱስም። ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ አለ።** በዚያም ስፍራ ብዙ ሣር ነበረበት። ወንዶችም ተቀመጡ ቊጥራቸውም አምስት ሺህ የሚያህል ነበር።

11 ኢየሱስም እንጀራውን ያዘ፥ አመስግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች ሰጡአቸው እንዲሁም ከዓሣው በፈለጉት መጠን። 12 ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን። አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው። 13 ሰለዚህ አከማቹ፥ ከበሉትም ከአምስቱ የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ።

14 **ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ። ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።** 15 በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ።

ብዙውን ጊዜ በነይማኖት ውስጥ ያሉትም የሌሉትም የሆነ ያገኙትን ነገር በቅርብ ከሚያውቁት ሰው፣ አካል፣ ወይም ነገር ጋር ያያይዙታል። እናም የሆነ ነገር ሲሰጣቸው፥ ይህን ነገር እገሌ ሰጠኝ ወይም ከእንትና አገኘሁት ብለው ያን ሰው ወይም አካል ያመሰግኑታል።

ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ "ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፤" ይለናል።

> መዝ.127:3 እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።

ታዲያ በእግዚአብሔር የሚያምኑትም የማያምኑትም ልጆችን ይወልዳሉ፤ ይህ ብቻ አይደለም የወለዱትን ልጁ ከአመኑበት አካል ጋር (ማን ይሁን ምን) አያይዘው ያን አካል ያከብሩበታል፥ ያመሰግኑበታል፥ ስጦታን ወይም ሰዕለትን ይሰጡታል ወዘተ. (ቅዱሳንን፣ መላእክትን፣ አላህን፣ ወይም ጠንቋይን ወዘተ ሊሆን ይችላል።)

ነገር ግን በሌላ ስፍራ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፥

> ሉቃ6:35 ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፥ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥ **እርሱ** (እግዚአብሔር) **ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና።** 36 አባታችሁ ሩኅሩኅ እንደ ሆነ ርኅሩኆች ሁኑ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ቸር ነውና ለፍጥረቱ ሁሉ መልካምን ያደርጋል። እኛንም ደግሞ እንደዛው እንድናደርግ ያዘናል።

ለምሳሌ ከላይ ያነበበውነውን ጥቅስ (ዮሐንስ 6፡5) ተመልከቱ፤ ኢየሱስ ዓይኑን አንስቶ ሕዝቡን ተመለከተ (ሁሉም በእምነት እየተከተሉት እንዳልነበሩ ከተለያዩ የወንጌል ክፍሎች ውስጥ ለመረዳት ትችላላችሁ። ለምሳሌ አንዳንዱ በሚናገረው ቃል ሊያጠምዱት ነበር የሚከተሉት።)

> ማር. 12:13 በንግግርም ሊያጠምዱት ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑትን ወደ እርሱ ላኩ።

እርሱ ግን ሕዝቡን አይቶ አዘነላቸው፥ በመልካም ሣር ላይም እንዲቀመጡ አዘዘና ጠግበው በልተው እስኪተርፋቸው ድረስ የሚበሉትንም ሰጣቸው።

ነገር ግን አሁን ላነሳው ያሰብሁት አንድ ነገር አለ፥ እግዚአብሔር ለሚለምኑት (ከላይ እንዳየነው ደግሞ ባይለምኑትም) ማድረግ የወደደውን ያደርጋል፤ ታዲያ ይህን ነገር በሚታዩም (በሰዎች…) ሆነ በማይታዩ ኃይላት ወይም አካላት (መላእክት፥ ወይም በራሱ) ሊያደርገው ይችላል።

ለምሳሌ ከላይ እንዳየነው ኢየሱስ ራሱ እየሄደ ለእያንዳንዳቸው በእጃቸው ዓሣውንና ዳቦውን አላከፋፈላቸውም፥ነገር ግን ለሐዋርያቱ ሰጣቸውና እነርሱ ለሕዝቡ አከፋፈሉት።

ሆኖም ግን ሰዎች በአብዛኛው ለማይታየውና ሁሉን ሰጪ ለሆነው አምላክ ክብርን ከመስጠት ይልቅ በሚታየው ወይም እነርሱ በሚያውቁት ላይ ያተኩራሉ።

> 26 ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። 27 **ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።** 28 እንግዲህ። የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት። 29 ኢየሱስ መልሶ። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።

ከዚህ ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ላይ ያለውን ተመልከቱ፤ እስራኤል ለኢየሱስ

> 30 እንግዲህ። እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? 31 “ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው” ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት።

ከጥቂት ሰዓታት (ምናልባት ደቂቃዎች) በፊት ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራ ወንዶች ብቻ ተቆጥረው ለአምስት ሺህ ሰዎች እንዲበቃ አድርጎ አበርክቶ እንደሰጣቸው አላስተዋሉም፤ “*ምን ምልክት ታደርጋለህ አሉት*” ለዚህም ይመስለኛል ኢየሱስ አስቀድሞ በቁጥር 26 ላይ “*የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁ ነው እንጂ ምልክት ስላያችሁ አይደለም*” ያላቸው።

ቀጥለውም በመዝሙር 78 ከቁጥር 24 ላይ የተጻፈውን “*ይበሉም ዘንድ መናን አዘነበላቸው፥ የሰማይንም እንጀራ ሰጣቸው።*” የሚለውን ቃል ጠቅሰው፥ ሙሴ እንደሰጣቸው አድርገው፥ አድርገው “*አንተስ ምን ምልክት ታደርጋለህ?*” አሉት። መልሱን ተመልከቱ፡

32 ኢየሱስም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ
ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤

እስራኤል በእርግጥም ሙሴ እርሱ ላከኝ ካላቸው ከእግዚአብሔር የልቅ ሙሴን እራሱኑ ነበር በልባቸው ያኖሩት። ለዚህም ይመስለኛል ሙሴ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በተራራ ላይ 10ሩን ትእዛዛት ይቀበል ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት በጾምና በጸሎት በቆየበት ጊዜ፥ አሮንን "*በፊታችን የሚሄዱ አማልክትን ሥራልን ያሉት*"

ዘጸ.32:1፤ ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው። ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት።

ኢየሱስ ንግግሩን ቀጥሎ፡

33 የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና
አላቸው። 34 **ስለዚህ። ጌታ ሆይ፥ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት።** 35 ኢየሱስም
እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ
የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።

አላቸው። ቀጥሎ ምን እንዳለ ታውቃለችሁ?

36 ነገር ግን አይታችሁኝ እንዳላመናችሁ አልኋችሁ።

ብዙዎቻችን በሕይወታችን ውስጥ እየሠራ ያለውን የእግዚአብሔር እጅ ሥራ እያየን እርሱን (እግዚአብሔርን) አለማመናችን ከምን የተነሳ ነው? ይባስ ብሎም እንደ እስራኤል በፊታችን ጣዖታትን አስቀምጠን ከእግዚአብሔር ፊታችንን ለምን መለስን?

37 አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ
አላወጣውም፤ 38 ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ
ከሰማይ ወርጃለሁና። 39 ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን
እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። 40 ልጅንም አይቶ በእርሱ
የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም
በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነ ሙሉነህ አዲሱ

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን። by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com